# ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት

## International Ethiopian Women's Organization

**IEWO,** ***P.O. Box 56729, Washington DC,***
**Please contact us at: Tel. 240 691-4370**
www.internationalethiopianwomenorganization.com

### ጋዜጣዊ መግለጫ

የካቲት 24 እና 25 ( March 3rd and 4th) የተደረገዉ የዓለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት ጉባአዔ በከፍተኛ ድምቀትና ተሳትፎ በተሳካ ሁኔታ ተካሂዷል።

በጉባኤዉ ላይ አኢሴድ የሚከተሉትን ዉሳኔዎች አስተላልፏል።

1. ጉባዔዉ በወቅታዊ የኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ ከተወያየ በኋላ ፤

ሀ) የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት በሕዝባችን ላይ በተለይም በሴቶችና በህጻናት ላይ የሚያደርገዉን የግፍ አገዛዝ አጥብቆ ተቃዉሟል።

ለ) ይሄንን የግፍ አገዛዝ ሊያስወግዱ ከሚችሉና ለፍትህ ርትዕ ከቆሙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች ጋር ለመተባበር ወስኗል።

2. ጉበዔዉ የኢትዮጵያ ሴቶች የሚገኙበትን ሁኔታ በመገምገም :-

ሀ) ኢትዮጵያዉያን ሴቶች ከመቸዉም በከፋ ሁኔታ ለድህነትና ለባርነት በመዳረጋቸዉ÷ አኢሴድ ይሄንን ሁኔታ ለማቃለል በማንኛቸዉም መንገድ የሚያስፈልገዉን ሁሉ ለማድረግ ወስኗል።

ለ) ይህ የግፍ አገዛዝ በፈጠረዉ ችግር ምክንያት እናቶችና፣ እህቶች በተለይም በመካከለኛዉ ምስራቅ መሰደዳቸዉንና ኢሰብአዊ በሆነ አኗኗር መሰቃየታቸዉን ባንክሮና በሃዘን ያስታዉስዋል ።

ሐ) ድርጅታችን አኢሴድ ብሶታቸዉን ለማሰማት በአለም አቀፍ የሰራተኞች ህግ በሚፈቅደዉ መሠረት መብታቸዉን የሚያስጠብቅ ግብረሀይል እንዲቋቋምም ወስኑዋል።

3. ጉባኤዉ ወጣቶችና ህጻናት ያላግባብ ከሀገራቸዉ በጉዲፈቻ መልክ መቸርቸራቸዉን በብረርቱ በመቃወም ዉሳኔያዎችን አሳልፋል ።

ሀ) የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት ለወደፊት የሚያመጣዉን ጉዳት ሳይመረምር ህፃናትን ለአደጋ አጋልጧል።
ለ) ጉባኤዉ ይህ ሁኔታ ልጆቻችንን ስቃይ ዉስጥ የዳረገዉ ለደህንነታቸዉ ታስቦ ባለመደረጉ መሆኑን ተገንዝቧል።

ለ)ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ አኢሴድ መፍትሄ የሚያስገኝ ጥናት ያካሂዳል።

4. ጉባዔዉ የኢትዮጵያ ሴቶች በሀገራቸዉ ጉዳይ ሙሉ ተሳታፊዎች ካልሆኑ ችግራችን ሊፈታ እንደማይችል በማወቅ፥ ሴቶች ወሳኝ ሚና ሊኖራቸዉ ይገባል ብሎ ያምናል።

ሀ) በመሆኑም አኢሴድ የኢትዮጵያ ሴቶች በፖለቲካ፥ በማህበራዊ ኑሮ፥ በኢኮኖሚና በባህል መስኮች ወደፊት የሚኖራቸዉን ብሔራዊ አስተዋፅዖ የሚያደርጉበትን መንገድ በተለያየ መድረክ ይከፍታል። ወጣቶችንም ያሰባስባል ያደራጃልም።

ለ) ለሀገር ለወገንና ለሴቶች ደህንነት እድገትና ብልጸግና ያመጣ ዘንድ ልዩ የምርምርና የጥናት እንዲሁም የትምህርት ዘርፍ ይፈጥራል።

5. ባለፉት ወራት የወያኔ መንግሥት ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የቀሰቀሰዉ ጦርነትና ግጭቶች ለሀገርና ለወገን ጥፋትን ብቻ የሚያተርፍ በመሆኑ አኢሴድ ያወግዛል።

6. ጉባዔዉ ሴቶች በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ያላቸዉን ቦታ ከመረመረና ከተወያዬ በኋላ ወደፊት ተገቢ ቦታቸዉን እንድይዙ አስፈላጊዉን ጥረት ያደርጋል፤፤ ለዚሁም ትምህርታዊ የሆኑ ታርካዊና ወቅታዊ ጽሁፎችን ያዘጋጃል።

7. ጉባኤዉ ኢትዮጵያ አገራችንና ሕዝቡዋ ከሃይማኖት ጋር ያለዉን መተሳሰር በመገንዘብ ኢትዮጵያዉያን የሃይማኖት መሪዎችና ተቁዋሞች ለሴቶች የሚገባዉን አስተዋጸኦና ሚና ማድረግ እንደሚገኝባቸዉ ያሳስባል።

የሃይማኖት ዋናዉ ሚና፥ ሕዝብን መጠበቅ ስለሆነ የሃይማኖት መሪዎችና ተቋሞች አሁንም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆሙ እንጅ ፤ ከወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት ጋር በመወገን ጸረ ኢትዮጵያ ጸረ ሕዝባችን ከሆነዉ ተግባር እንዲወገዱ አጥብቆ ያሳስባል።

8. አኢሴድ በዉጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንም የተለያዩ ማሕበራዊ አገልግሎት በማዘጋጀት ፤ የጤናና፥ ትምህርታዊ ምክሮችን በመስጠት በዚህ ዙርያ ያሉ አገልግሎቶችን ማበርከት አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል።

9. ጉባዔዉ የሰብዓዊ መብት ረገጣን በተመለከተ፤የወያኔ ኢሕአዴግን ሥርዓት ይኮንናል። የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች በሙሉ ፤ ጋዜጠኞችም ባስቸኳይ ኢንዲፈቱ ይጠይቃል።

ዋሽንግቶን ዲሲ የካቲት 25 ቀን 1999 ዓ ም